
# ልሳነ ግእዝ

## ሁለተኛ ክፍል



[illegible]

[illegible]

## መግቢያ (ሙባዕ)

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ቋንቋዎች ባለቤት ስትኾን የግእዝ ቋንቋ ከቀደምት ቋንቋዎች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡ የግእዝ ቋንቋ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ ለረጅም ዘመናት ያገለገለ ሲኾን ለሀገራችን የሥነ ጽሑፍ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በመሆኑም አያሌ ቅዱሳት መጻሕፍት የጥበብ መጻሕፍት የታሪክ መዛግብት እንዲሁም ጥንታውያን ቅኔያት የተጻፉት በግእዝ ቋንቋ በመኾኑ ቤተ ክርስቲያናችንን ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያን እንዲኹም የአባቶቻችንን ጥንታውያን ጥበቦች ለመረዳት የግእዝን ቋንቋ ማወቅ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው፡፡

አባቶቻችን ልጆቻቸውን በመንፈሳዊ ዕውቀት እና ሥነ ምግባር በማነጽ ለቤተክርስቲያን እና ለሀገራችን ተተኪ ትውልድን እያፈሩ እዚህ ካለንበት ዘመን ደርሰናል፡፡ ከነዚኽም የማስተማር ጥበባት አንዱ የቃል ትምህርት ሲኾን ይህ ትምህርት ልጆች የጸሎት መጻሕፍትን በቃል እየተነገራቸው እነርሱም ደጋግመው በመናገር ቃላቱን እንዲይዙ እና ጸሎታቸውን በቃላቸው ማድረስ እንዲችሉ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ትምህርት ከአባቶቻችን የወረስነውን የማስተማር ጥበብ በመከተል ቤተክርስቲያንን የሚረከቡ ካህናትን እና ምእመናን ለማፍራት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

# መክስተ ርዕስ (ይዘት)

## አርእስት

ምዕራፍ አሐዱ

፩.፩ የአንደኛ ክፍል ክለሣ ፩

፩.፪ የግእዝ አኃዝ ከ፶፩-፲፻ ፪

፩.፫ የዮሐንስ ወንጌል ንባብ በግእዝ ውርድና ቁም ንባባት

(ምዕራፍ ፩÷፩-፲) ፰

ምዕራፍ ክልኤቱ

፪.፩ መራሕያን ፲፮

፪.፪ የዮሐንስ ወንጌል ንባብ በግእዝ ውርድና ቁም ንባባት

(ምዕራፍ ፩÷፲፩-፳) ፲፰

ምዕራፍ ሠለስቱ

፫.፩ የቤተሰብ ዝርዝር ፳፪

፫.፪ የዮሐንስ ወንጌል ንባብ በግእዝ ውርድና ቁም ንባባት

(ምዕራፍ፩÷፳፩-፴) ፳፪

ምዕራፍ አርባዕቱ

፬.፩ የአካል ክፍሎች ፳፮

፬.፪ የዮሐንስ ወንጌል ንባብ በግእዝ ውርድና ቁም ንባባት

(ምዕራፍ፩÷፴፩-፵) ፳፰

ምዕራፍ ኀምስቱ

፭.፩ ቀለማት ፴፪

፭.፪ አልባሳት ፴፬

፭.፫ ትዕምርተ መካናት ፴፭

ዋቢ መጻሕፍት ፴፮

# የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ተምረው ሲያጠናቅቁ፡

- በግእዝ የተጻፈ የጸሎት መጽሐፍ ማንበብ ይችላሉ።
- ዮሐንስ ወንጌልን የግእዝ ሥርዓተ ንባብን ተከትለው ያነባሉ።
- የቤተሰብ አካላት የግእዝ ስያሜ ዐውቀው በዕለት ተዕለት ውሎአቸው ይጠቀሙበታል።
- የሰውነት አካላቸውን ስያሜ ዐውቀው በዕለት ተዕለት ውሎአቸው ይጠቀሙበታል።
- የግእዝ ቁጥሮችን ዐውቀው ያነባሉ በእነርሱ ይጽፋሉ።
- ቃላትን በማጥናት የግስ ዕውቀት ሀብታቸውን ያበለጽጉበታል።

# ምዕራፍ አሐዱ
## ክለሣ ዘቀዳማይ ክፍል

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦
. ቁጥሮችን በግእዝ ይለያሉ
. ቁጥሮችን በግእዝ ለይተው ይጽፋሉ

### ተስእሎታተ መራኁት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. 99 ን በግእዝ አኀዝ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።
፪. መልእክተ ዮሐንስን ለመምህራቹ በቃል በሉሎቸው።
፫. የግእዝ መራሕያን የሚባሉት ስንት ናቸው?

እፎ ሀሎክሙ አርድእተ ግእዝ ዘካልአይ ክፍል በዘንለፈ ክፍለ ትምህርት አንትሙ ተመሀርክሙ በይነ ፊደላት ወኍልቄ አኃዛት ዘግእዝ ወመራሕያን ። በይነዝ እምቅድመ ንውጥን ትምህርት ዘካልአይ ክፍል ንድግም ዘንተ ትምህርት ከመ ይኩንነነ ብሩሀ (የሁለተኛ ክፍል የግእዝ ተማሪዎች እንደምን አላችሁ ባለፈው ክፍል ስለ ፊደላት፣የግእዝ ቁጥሮች እና መራሕያንም ተምራችኋል። በዚሁ ምክንያት የሁለተኛ ክፍል ትምህርታችንን ከመጀመራችን አስቀድሞ ያለፈው ትምህርት ግልጽ እንዲሆንልን እንከልሳለን።)

## ፩.፩ የግእዝ ፊደላት ክለሣ

መምህር የግእዝ እና የአማርኛ ፊደላትን እንዲያስታውሷቸው በረድፍ ደርድረው ያሳየዋቸው።

## ፩.፪ የግእዝ ቁጥሮች ክለሣ

መምህር የግእዝ ቁጥሮችን ጽፈውላቸው በግእዝ እንዲያነቡ እና የአማርኛ አቻቸውን እንዲጽፉ ያድርጓቸው።

## ፩.፫ የግእዝ መራሕያን ክለሣ

መምህር የግእዝ መራሕያንን ቍጥራቸውን እና ዝርዝራቸውን በየተራ እያስነሱ ተማሪዎቹን ይጠይቋቸው።

## ፩.፬ የቤተሰብ ዝርዝር ክለሣ

መምህር የተለያ የቤተሰብ አባላትን በአማርኛ እያሉላቸው አቻ የግእዝ ፍቺያቸውን እንዲናገሩ ለተማሪዎቹ እድል ይስጡ።

## ፩.፭ የግእዝ አኃዝ ከ ፻-፻፶

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፻ወ፩ | ምእት ወአሐዱ | 101 | አንድ መቶ አንድ |
| ፻ወ፪ | ምእት ወክልኤቱ | 102 | አንድ መቶ ሁለት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፻ወ፫ | ምእት ወሠለስቱ | 103 | አንድ መቶ ሦስት |
| ፻ወ፬ | ምእት ወአርባዕቱ | 104 | አንድ መቶ አራት |
| ፻ወ፭ | ምእት ወኀምስቱ | 105 | አንድ መቶ አምስት |
| ፻ወ፮ | ምእት ወስድስቱ | 106 | አንድ መቶ ስድስት |
| ፻ወ፯ | ምእት ወሰብዓቱ | 107 | አንድ መቶ ሰባት |
| ፻ወ፰ | ምእት ወሰመንቱ | 108 | አንድ መቶ ስምንት |
| ፻ወ፱ | ምእት ወተስዓቱ | 109 | አንድ መቶ ዘጠኝ |
| ፻ወ፲ | ምእት ወዐሠርቱ | 110 | አንድ መቶ አስር |
| ፻ወ፳ | ምእት ወዕሥራ | 120 | አንድ መቶ ሃያ |
| ፻ወ፴ | ምእት ወሠላሳ | 130 | አንድ መቶ ሠላሳ |
| ፻ወ፵ | ምእት ወአርብዓ | 140 | አንድ መቶ አርባ |
| ፻ወ፶ | ምእት ወኀምሳ | 150 | አንድ መቶ ሀምሳ |

## ፩.፮ የግእዝ አኃዝ ከ ፻፶-፪፻

| የግእዝ ቁጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቁጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቁጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፻ወ፶ | ምእት ወኀምሳ | 150 | አንድ መቶ ሀምሳ |
| ፻ወ፷ | ምእት ወስድሳ/ ስሳ | 160 | አንድ መቶ ስልሳ |
| ፻ወ፸ | ምእት ወሰብዓ | 170 | አንድ መቶ ሰባ |
| ፻ወ፹ | ምእት ወሰማንያ | 180 | አንድ መቶ ሰማንያ |
| ፻ወ፺ | ምእት ወተስዓ | 190 | አንድ መቶ ዘጠና |
| ፪ወ፻ | ክልኤቱ ምእት | 200 | ሁለት መቶ |

## ፩.፯ የግእዝ አኃዝ ከ፪፻-፫፻

| የግእዝ ቁጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቁጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቁጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፪ወ፻ | ክልኤቱ ምእት | 200 | ሁለት መቶ |
| ፪፻ወ፲ | ክልኤቱ ምእት ወዐሠርቱ | 210 | ሁለት መቶ አሥር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፪፻ወ፳ | ክልኤቱ ምእት ወዕሥራ | 220 | ሁለት መቶ ሃያ |
| ፪፻ወ፴ | ክልኤቱ ምእት ወሠላሳ | 230 | ሁለት መቶ ሠላሳ |
| ፪፻ወ፵ | ክልኤቱ ምእት ወአርብዓ | 240 | ሁለት መቶ አርባ |
| ፪፻ወ፶ | ክልኤቱ ምእት ወኀምሳ | 250 | ሁለት መቶ ሃምሳ |

## ፩.፬ የግእዝ አኃዝ ከ፪፻፶-፫፻

| የግእዝ ቁጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቁጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቁጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፪፻ወ፶ | ክልኤቱ ምእት ወሃምሳ | 250 | ሁለት መቶ ሀምሳ |
| ፪፻ወ፷ | ክልኤቱ ምእት ወስድሳ/ ስሳ | 260 | ሁለት መቶ ስልሳ |
| ፪፻ወ፸ | ክልኤቱ ምእት ወሰብዓ | 270 | ሁለት መቶ ሰባ |
| ፪፻ወ፹ | ክልኤቱ ምእት ወሰማንያ | 280 | ሁለት መቶ ሰማንያ |
| ፪፻ወ፺ | ክልኤቱ ምእት ወተስዓ | 290 | ሁለት መቶ ዘጠና |
| ፫ወ፻ | ሠለስቱ ምእት | 300 | ሦስት መቶ |

## ፩.፭ የግእዝ አኃዝ ከ፫፻-፫፻፺፩+፱

| የግእዝ ቁጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቁጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቁጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፫ወ፻ | ሠለስቱ ምእት | 300 | ሦስት መቶ |
| ፫፻ወ፲ | ሠለስቱ ምእት ወዐሠርቱ | 310 | ሦስት መቶ አስር |
| ፫፻ወ፳ | ሠለስቱ ምእት ወዕሥራ | 320 | ሦስት መቶ ሃያ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፫፻ወ፴ | ሠለስቱ ምእት ወሠላሳ | 330 | ሦስት መቶ ሠላሳ |
| ፫፻ወ፵ | ሠለስቱ ምእት ወአርብዓ | 340 | ሦስት መቶ አርባ |
| ፫፻ወ፶ | ሠለስቱምእት ወኀምሳ | 350 | ሦስትመቶሓምሳ |

## ፩.፯ የግእዝ አኃዝ ከ፫፻፶-፬፻

| የግእዝ ቊጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቊጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቊጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፫፻ወ፶ | ሠለስቱ ምእት ወኀምሳ | 350 | ሦስት መቶ ሓምሳ |
| ፫፻ወ፷ | ሠለስቱ ምእት ወስሳ | 360 | ሦስት መቶ ስልሳ |
| ፫፻ወ፸ | ሠለስቱ ምእት ወሰብዓ | 370 | ሦስት መቶ ሰባ |
| ፫፻ወ፹ | ሠለስቱ ምእት ወሰማንያ | 380 | ሦስት መቶ ሰማንያ |
| ፫፻ወ፺ | ሠለስቱ ምእት ወተስዓ | 390 | ሦስት መቶ ዘጠና |
| ፬ወ፻ | አርባዕቱ ምእት | 400 | አራት መቶ |

## ፩.፰ የግእዝ አኃዝ ከ ፬፻፲-፬፻፶

| የግእዝ ቊጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቊጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቊጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፬፻ወ፲ | አርባዕቱ ምእት ወዐሠርቱ | 410 | አራት መቶ አስር |
| ፬፻ወ፳ | አርባዕቱ ምእት ወዕሥራ | 420 | አራት መቶ ሃያ |
| ፬፻ወ፴ | አርባዕቱ ምእት ወሠላሳ | 430 | አራት መቶ ሠላሳ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፬፻ወ፵ | አርባዕቱ ምእት ወአርብዓ | 440 | አራት መቶ አርባ |
| ፬፻ወ፶ | አርባዕቱ ምእት ወኀምሳ | 450 | አራት መቶ ሃምሳ |

## .፰ የግእዝ አኃዝ ከ ፬፻፶-፭፻

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፬፻ወ፶ | አርባዕቱ ምእት ወኀምሳ | 450 | አራት መቶ ሓምሳ |
| ፬፻ወ፷ | አርባዕቱ ምእት ወስሳ | 460 | አራት መቶ ስልሳ |
| ፬፻ወ፸ | አርባዕቱ ምእት ወሰብዓ | 470 | አራት መቶ ሰባ |
| ፬፻ወ፹ | አርባዕቱ ምእት ወሰማንያ | 480 | አራት መቶ ሰማንያ |
| ፬፻ወ፺ | አርባዕቱ ምእት ወተስዓ | 490 | አራት መቶ ዘጠና |
| ፭ወ፻ | ኀምስቱ ምእት | 500 | አምስት መቶ |

## ፩.፱ የግእዝ አኃዝ ከ ፭፻-፭፻፶

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፭ወ፻ | ኀምስቱ ምእት | 500 | አምስት መቶ |
| ፭፻ወ፲ | ኀምስቱ ምእት ወዐሠርቱ | 510 | አምስት መቶ አስር |
| ፭፻ወ፳ | ኀምስቱ ምእት ወዕሥራ | 520 | አምስት መቶ ሃያ |
| ፭፻ወ፴ | ኀምስቱ ምእት ወሰላሳ | 530 | አምስት መቶ ሠላሳ |
| ፭፻ወ፵ | ኀምስቱ ምእት ወአርብዓ | 540 | አምስት መቶ አርባ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፭፻ወ፶ | ኀምስቱ ምእት ወኀምሳ | 550 | አምስት መቶ ኀምሳ |

## ፩.፲ የግእዝ አኃዝ ከ ፭፻፶-፮፻

| የግእዝ ቁጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቁጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቊጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፭፻ወ፶ | ኀምስቱ ምእት ወኀምሳ | 550 | አምስት መቶ ኀምሳ |
| ፭፻ወ፷ | ኀምስቱ ምእት ወስሳ | 560 | አምስት መቶ ስልሳ |
| ፭፻ወ፸ | ኀምስቱ ምእት ወሰብዓ | 570 | አምስት መቶ ሰባ |
| ፭፻ወ፹ | ኀምስቱ ምእት ወሰማንያ | 580 | አምስት መቶ ሰማንያ |
| ፭፻ወ፺ | ኀምስቱ ምእት ወተስዓ | 590 | አምስት መቶ ዘጠና |
| ፮ወ፻ | ስድስቱ ምእት | 600 | ስድስት መቶ |

## ፩.፲፩ የግእዝ አኃዝ ከ ፮፻-፮፻፶

| የግእዝ ቊጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቊጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቊጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፮ወ፻ | ስድስቱ ምእት | 600 | ስድስት መቶ |
| ፮፻ወ፲ | ስድስቱ ምእት ወዐሠርቱ | 810 | ስድስት መቶ አስር |
| ፮፻ወ፳ | ስድስቱ ምእት ወዕሥራ | 620 | ስድስት መቶ ሃያ |
| ፮፻ወ፴ | ስድስቱ ምእት ወሰላሳ | 630 | ስድስት መቶ ሠላሳ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፮፻ወ፵ | ስድስቱ ምእት ወአርብዓ | 640 | ስድስት መቶ አርባ |
| ፮፻ወ፶ | ስድስቱ ምእት ወኀምሳ | 650 | ስድስት መቶ ኀምሳ |

## ፩.፲፪ የግእዝ አኃዝ ከ፮፻፶-፯፻

| የግእዝ ቊጥሮች በ**አኃዝ** | የግእዝ ቊጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቊጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፮፻ወ፶ | ስድስቱ ምእት ወኀምሳ | 650 | ስድስት መቶ ሓምሳ |
| ፮፻ወ፷ | ስድስቱ ምእት ወስሳ | 660 | ስድስት መቶ ስልሳ |
| ፮፻ወ፸ | ስድስቱ ምእት ወሰብዓ | 670 | ስድስት መቶ ሰባ |
| ፮፻ወ፹ | ስድስቱ ምእት ወሰማንያ | 680 | ስድስት መቶ ሰማንያ |
| ፮፻ወ፺ | ስድስቱ ምእት ወተስዓ | 690 | ስድስት መቶ ዘጠና |
| ፯ወ፻ | ስብዓቱ ምእት | 700 | ሰባት መቶ |

## የምዕራፍ ፩ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ሀ) አርድእት ለዘይተልዉ ተስእሎታት ሀቡ ሚጠተ ለእመ ኮነ ርቱዐ በሉ አማነ ወለእመ ኢኮነ አማነ በሉ ሐስወ፡፡

፩) ፱፻፺፪ የዐረብኛ አቻው 9192 ነው፡፡

፪) የግእዝ ፊደላት ብዛት ፳፮ ነው፡፡

፫) መራሕያን ቊጥራቸው ፲ ነው፡፡

### ለ) አርድእት ኅርዩ ርቱዐ አውስኦተ እምነ ዘተውሕቡ፡፡

፫) ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ________ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል፡፡ ባዶ ቦታ ላይ የሚገባው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ) ውእቱ ለ) ወውእቱ ቃል ሐ) ዘተፈነወ መ) እም ኀበ እግዚአብሔር

፬) 969 ቊጥር በግእዝ በትክክል የተጻፈው የቱ ነው?

ሀ) ፱፻፷፱ ለ) ፱፻ ሐ)፱፻፷ መ)፱፻፷፫

፭) ከሚከተሉት ቊጥሮች ሠለስቱ ምዕት ወሠላሳ ተብሎ የሚነበበው የግእዝ ቁጥር የትኛው ነው?

ሀ) ፴፻፴ ለ) ፴፻፴፱ ሐ) ፫፻፴ መ) ፻፴፫

### ሐ) ሀቡ ድልወ አውስኦተ ለዘይጠልዉ ተስእሎታት፡፡

፩) የግእዝ ፊደላት ስንት ናቸው?

፪) የዮሐንስ ወንጌል ምን ብሎ ይጀምራል?

# ምዕራፍ ክልኤቱ
## መራሕያን

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

አሥሩን መራሕያን ይለያሉ፤
የመራሕያን ክፍሎችን ያውቃሉ፤

### ተስእሎታተ መራኅት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩) ተማሪዎች መራሕያን ማለት ምን ማለት ነው?
፪) በቁጥር ስንት እንደሆኑ ለመምህራችሁ ነግራችሁ ሁሉንም ጻፉ።

## መራሕያን

መራሕያን ማለት መርሐ መራ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን መራሕያን ማለት መሪዎች ማለት ነው፡፡ እነዚህም መራሕያን የምንላቸው ተውላጠ ስሞችን ነው፡፡ ተውላጠ ስም መባላቸውም ስምን ለውጠው በስም ምትክ አየገቡ እንደባለቤት የሚያገለግሉ ስለሆኑ ነው፡፡

እነዚህ የግእዝ መራሕያን ብዛታቸው ፲(ዐሥር) ሲሆን በ፬(አራት) መሠረታዊ የተግባር ክፍል ይመደባሉ፡፡

የግእዝ መራሕያን የሚባሉት

፩. አነ= እኔ

፪. ንሕነ= እኛ

፫. አንተ= አንተ

፬. አንቲ= አንቺ

፭. አንትሙ= እናንተ (ለወንዶች)

፮. አንትን= እናንተ (ለሴቶች)

፯. ውእቱ= እርሱ

፰. ይእቲ= እርሷ

፱. ውእቶሙ= እነርሱ (ለወንዶቹ)

፲. ውእቶን= እነርሱ(ለሴቶች)

## የመራሕያን ክፍሎች

በ፬ (አራት) መሠረታዊ የተግባር ክፍል የሚባሉት

፩. የመደብ ክፍሎች

፪. የፆታ ክፍሎች

፫. የቍጥር ክፍሎች

፬. የድርጊት ክፍሎች

## የመደብ ክፍሎች

መራሕያን በመደብ ሲከፋፈሉ በሦስት መሠረታዊ መደቦች ይከፈላሉ። እነርሱም

### ፩ኛ መደብ

አነ

ንሕነ

### ፪ኛ መደብ

አንተ

አንቲ

አንትሙ

አንትን

### ፫ኛ መደብ

ውእቱ

ይእቲ

ውእቶሙ

ውእቶን

## የፆታ ክፍሎች

መራሕያን በፆታ ሲከፋፈሉ በሦስት ይመደባሉ።

### ፩ኛ- የወንድና የሴት ፆታ አመልካቾች

አነ

ንሕነ

### ፪ኛ- የወንድ ፆታ አመልካች

አንተ

ውእቱ

አንትሙ

ውእቶሙ

### ፫ኛ- የሴት ፆታ አመልካች

ይእቲ

አንቲ

አንትን

ውእቶን

**የቍጥር ክፍሎች**

መራሕያን በቁጥር ሲከፋፈሉ በ ሁለት ዐቢይ ክፍል ይከፈላሉ

**፩ኛ- ነጠላ ቁጥር አመልካች**

አነ

አንተ

ውእቱ

ይእቲ

አንቲ

**፪ኛ- ብዙ ቍጥር አመልካች**

ንሕነ

አንትሙ

አንትን

ውእቶሙ

ውእቶን

**የድርጊት ክፍሎች**

መራሕያን በድርጊት ሲከፋፈሉ በሦስት መሠረታዊ ድርጊቶች ይከፋፈላሉ። እነርሱም

**፩ኛ- የቅርብና የሩቅ ድርጊት አመልካቾች**

አነ

ንሕነ

**፪ኛ- የቅርብ ድርጊት አመልካቾች**

አንተ

አንቲ

አንትሙ

አንትን

**፫ኛ- የሩቅ ድርጊት አመልካቾች**

ውእቱ

ይእቲ

ውእቶሙ

ውእቶን

## የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፩፥፲፩-፳

## ምዕራፍ ፩

፲፩. ውስተ ዚአሁ መጽአ ወእሊአሁሰ ኢተወክፍዎ::

፲፪. ወለእለሰ ተወክፍዎ ወሀቦሙ ሥልጣነ ውሉደ እግዚአብሔር ይኩኑ ለእለ አምኑ በስሙ::

፲፫. እለ ኢኮኑ እምነ ዘደም ወኢእምፈቃደ ፍትወት ዘሥጋ ወኢእምሥምረተ ብእሲ አላ እምእግዚአብሔር ተወልዱ::

፲፬. ወውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐተ አሐዱ ዋሕድ ለአቡሁ ዘምሉእ ጸጋ ወሞገሰ ወጽድቀ::

፲፭. ወዮሐንስ ስምዐተ ኮነ በእንተ ክርስቶስ ከሠተ አፉሁ እንዘ ይብል፡እም ድኅሬየ ዘይመጽዕ ውእቱ ሁሎ ቅድመ ዚአየ ወከብረ እም አነ ዝ ውእቱ ዘተናበብኩ በቀዳሚ::

፲፮. እስመ እምተረፈ ዚአሁ ነሣእነ ንሕነ ኵልነ ጸጋ ህየንተ ጸጋ በዲበ ጸጋ::

፲፯. እስመ ኦሪት በሙሴ ተውህበት ለነ ወጸጋሰ ወጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ኮነ::

፲፰. ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ አላ ወልድ ዋሕድ ዘሀሎ ውስተ ሕፅነ አቡሁ ውእቱ ነገረነ ::

፲፱. ወዝንቱ ውእቱ ስምዑ ለዮሐንስ አመ ለአኩ ኀቤሁ አይሁድ እምኢየሩሳሌም ካህናተ ወሌዋውያነ ከመ ይሰአልዎ ወይበልዎ አንተአ መኑ አንተ ::

፳. ወአምነ ወኢክሕደ ወአምነ ከመ ኢኮነ ውእቱ ክርስቶስሃ ::

## የምዕራፍ ፪ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ሀ) አርድዕት ለዘይተልዉ ተስእሎታት ለእመ ኮኑ አማን በሉ ርቱዕ ወለእመ ኢኮኑ አማን በሉ ሕስው።

፩) መራሕያን በ፬ መሠረታዊ የተግባር ክፍሎች ይከፈላሉ።

፪) የቅርብ ድርጊት አመልካቾች ከመደብ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው።

፫) አነ የነጠላ ቊጥር አመልካች ነው።

### ለ) አርድእት ኅርዩ ርቱዐ አውስኦተ እምነ ዘተውሕቡ።

፩) መራሕያን በስንት መሠረታዊ የተግባር ክፍሎች ይከፈላሉ?

ሀ) ፬ ለ) ፫ ሐ) ፳ መ) ፪

፪) ከሚከተሉት ውስጥ የሩቅ ድርጊት አመልካቾች የሆነው የቱ ነው?

ሀ) አንትሙ ለ)ውእቶሙ ሐ) አንተ መ)ንሕነ

፫) ከሚከተሉት ውስጥ ፪ መደብ የሖነው የቱ ነው?

ሀ) አንተ ለ) አንቲ ሐ) አንትሙ መ) አንትን

### ሐ) ሀቡ ድልወ አውስኦተ ለዘይተልዉ ተስእሎታት።

፩) መራሕያን በፆታ ሲከፋፈሉ ስንት ናቸው? ዝርዝራቸውን ጻፉ።

# ምዕራፍ ሠለስቱ
# የቤተሰብ ዝርዝር

## የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኂላ፦

. የቤተሰብ አካላት በግእዝ ምን ተብለው እንደሚጠሩ ይለያሉ፤
. እነርሱም ቤተሰቦቻቸውን በግእዝ መጠርያ ይጠራሉ፤

## ተስእሎታተ መራኁት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. ተማሪዎች ካለፈው ምእራፍ በመነሳት በዚህኛው ምዕራፍ ምን ታሪክ እናነባለን ብላችሁ አሰባችሁ?
፪. የምዕራፍ አምስትን የመጀመሪያዎቹን ሁለት አንቀጾች ለመምህራችሁ በውርድ እና በቁም ንባብ አንብቡላቸው።

## አስማተ ሰብአ ቤት

አብ= አባት

እም= እናት

ወልድ= ወንድ ልጅ

ወለት= ሴት ልጅ

ዱድ= አጎት

ዱዲት= አክስት

ሐው= ወንድ አያት

ሐውት= ሴት አያት

እምሐው= ወንድ ቅድመ አያት

እምሐውት= ሴት ቅድመ አያት

እኁ = ወንድም

እኅት= እኅት

ብእሲ= ባል

ብእሲት= ሚስት

አርክ (ቢጽ)= ጓደኛ

ጎር= ጎረቤት

እደው= ወንዶች

አንስት= ሴቶች

## የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፩፥፳፩-፴

### ምዕራፍ ፩

፳፩. ወይቤልዎ መኑአ አንተ ኤልያስኑ አንተ:: ወይቤ ኢኮንኩ:: ወይቤልዎ ነቢይኑ አንተ:: ወይቤ አልቦ::

፳፪. ወይቤልዎ መኑመ አንተ እንከ ከመ ናይድዖሙ ወናጠይቆሙ ለእለ ለአኩነ:: መነ ትብል ርእሰከ::

፳፫. ወይቤ አንሰ ቃለ ዐዋዲ ዘይሰብክ በገደም ወይብል ጺሑአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር በከመ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ::

፳፬.ወእለሰ ተፈነዉ እምፈሪሳውያን አሙንቱ::

፳፭.ወተስእልዎ ወይቤልዎ በእፎ እንከ ታጠምቅ ለእመ ኢኮንከ ክርስቶስሃ ወኢአልያስሃ

ወኢነቢየ።

፳፮. ወአውሥአ ዮሐንስ ወይቤሎሙ አንሰ አጠምቀክሙ በማይ ወማእከሌክሙ ሀሎ ይቀውም ዘኢታአምርዎ አንትሙ።

፳፯. ዘይመጽእ እምድኅሬየ ወውእቱ ዘሀሎ እምቅድሜየ ዘኢይደልወነ እፍታሕ ቶታነ አሣዕኒሁ እምእገሪሁ ወውእቱ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወበእሳት።

፳፰. ወከመዝ ኮነ በቢታንያ በቤተራባ በማዕዶተ ዮርዳኖስ በኀበ ሀሎ ያጠምቅ ዮሐንስ።

፳፱. ወአመ ሳኒታ ርእዮ ዮሐንስ ለኢየሱስ እንዘ ይመጽእ ኀቤሁ ወይቤ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያአትት ኀጢአት ዓለም።

፴. ዝንቱ ውእቱ ዘእቤለክሙ አነ በእንቲአሁ ይመጽእ እምድኅሬየ ብእሲ ዘሀሎ እምቅድሜየ እስመ እምቅድሜየ ውእቱ ኮነ።

## የምዕራፍ ፫ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ) አርድእት ለዘይተልዉ ተስእሎታት ለእመ ኮኑ አማነ በሉ ርቱዐ ወለእመ ኢኮኑ አማነ በሉ ሕስው።

፩) ጓደኛ የግእዝ ቋንቋ አቻው ቢጽነው።

፪)የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ቁጥር ሠላሳ "ዘይመጽእ እምድኅሬየ"ብሎ ይጀምራል።

፫)እም ሔውት ማለት ወንድ ቅድመ አያት ማለት ነው።

ለ) አርድእት ኅርዩ ርቱአ አውስኦት እምነ ዘተውሕቡ።

፩) ጓደኛ በግእዝ ቋንቋ_______________ነው።

ሀ) ቢጽ ለ)አርክ ሐ) ዱዲት መ) ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

፪) የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ቁጥር ሃያ ስምንትምንብሎ ይጀምራል?

ሀ) ወከመዝ ኮነ ለ) ወአመ ሳኒታ ሐ) ዘይመጽእ መ) ወአውሥአ

፫) ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ "ወልድ" ለሚለው ቃል አቻ ፍቺው ምንድነው?

ሀ) አኀት ለ) ባል ሐ) ኀረቤት መ) ወንድ ልጅ

ሐ) ሀቡ ድልው አውስኦት ለዘይተልዉ ተስእሎታት።

፩) ወልጡ ኀበ ልሳነ አምሃራ።

እደው=__________________

እኀት=__________________

ወለት=__________________

ሔው=__________________

እም=__________________

አብ=__________________

# ምዕራፍ አርባዕቱ
# የአካል ክፍሎች በግእዝ

## የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

. የሰውነት ክፍሎችን በግእዝ ምን ተብለው እንደሚጠሩ ይለያሉ
. የሰውነት ክፍሎቻቸውን በግእዝ ይጠራሉ

## ተስእሎታተ መራኁት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. እጅ በግእዝ ቋንቋ ምን ይባላል?

፪. ልሳን ማለት ምን ማለት ነው?

## አስማተ አካላተ ሰብእ

ሰብእ ብሂል እም አርባእቱ ባሕርያተ ሥጋ ወእም ሠልስቱ ባሕርያት ነፍስ በአርአያ ሥላሴ ፍጡር ውእቱ (ሰው ማለት ከአራቱ የሥጋ ባህሪያት እና ከሦስቱ የነፍስ ባሕሪያት በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ነው።

### አካላት ዘላዕለ ክሳድ፡- የአንገት በላይ አካል

ርእስ= ራስ

ድማኅ = መሐል ራስ

ናላ = አናት

ስእርት = የራስ ፀጉር

ጽፍሮ = ሹሩባ

ድንጉዝ = ጥቅል ሥራ

ድምድማ = የተበጠረ ጎፈሬ

ሲበት= ሽበት

ገጽ = ፊት

ፍጽም = ግንባር

ቅርንብ = ቅንድብ

ዓይን = ዓይን

ምጕንጳ = የዓይን ሽፋን

እዝን = ጆሮ

መልታህ = ጉንጭ

ከንፈር = ከንፈር

አፍ = አፍ

አንፍ = አፍንጫ

መንሰከ = መንጋጋ

ትናግ = ላንቃ

ልሳን = ምላስ

ጉርኤ = ጉሮሮ

ሕልቅ = አገጭ

ጽሕም = ጢም

ክሳድ = አንገት

ስን = ጥርስ

## አካል ዘታህተ ክሳድ - የአንገት በታች የካል ክፍሎች

መትከፍት = ትከሻ

ዘባን = ጀርባ

እንግድአ = ደረት

እድ = እጅ

መዝራዕት = መዳፍ

እመት = ክንድ

እራሕ = መሃል እጅ

አጽብዕት = ጣት

ጽፍር = ጥፍር

አጽባዕተ እድ = የእጅ ጣት

ጥብዕ = ጡት

ገቦ = ጎን

ሕፅን = ብብት

ከርሥ = ሆድ

ልብ = ልብ

ኵርናዕ = ክርን

አማዑት = አንጀት

ኵሊት = ኩላሊት

ቍይጽ = ጭን

ብረክ = ጉልበት

ካቢ = የእግር ባት

አንጉዕ = ቅልጥም

እግር = እግር

አጽባዕተ እግር = የእግር ጣት

ሰኰና = ተረከዝ

መከየድ = መርገጫ(ጫማ)

ዓጽም = አጥንት

ደም = ደም

ሕዋስ = ሰውነት

አምትንት = ቋንጃ

መትን = ትልቁ ጅማት

መሳውዕ = ጅማት

ሕንብርት = እንብርት

ሐሞት = አሞት

## የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፩፥፴፩-፵

## ምዕራፍ ፩

፴፩. ወአንሰ ኢያአምሮ ዳእሙ ከመ ያእምርዎ እስራኤል በእንተዝ መጻእኩ አነ ከመ አጥምቅ በማይ ::

፴፪. ወነገረ ስምዖ ዮሐንስ ወይቤ ርኢኩ መንፈሰ ቅዱስ እንዘ ይወርድ እምሰማይ ከመ እንተ ርግብ ወነበረ ዲቤሁ::

፴፫. ወአንሰ ኢያአምሮ ወባሕቱ ዘፈነወኒ ከመ አጥምቅ በማይ ውእቱ ይቤለኒ ዲበ ዘርኢከ ይወርድ መንፈስ ቅዱስ ወይነብር ዲቤሁ ውእቱኬ ዘያጠምቅ በመንፈስ ቅዱስ::

፴፬. ወለሊየ ርኢኩ ወአነ ሰማዕቱ ከመ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለእግዚአብሔር ::

፴፭. ወበሳኒታ ካዕበ እንዘ ይቀውም ዮሐንስ ወክልኤቱ እምአርዳኢሁ::

፴፮. ርእይዎ ለኢየሱስ እንዘ የሐውር ወይቤ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያአትት ኃጢአተ ዓለም::

፴፯. ወሰምዕዎ ክልኤሆሙ አርዳኢሁ እንዘ ይብል ከመዝ ወተለውዎ ለኢየሱስ::

፴፰. ወተመይጠ ኢየሱስ ርእዮሙ እንዘ ይተልውዎ ወይቤሎሙ ምንተ ተኀሥሡ::

፴፱. ወይቤልዎ ረቢ ዘበትርጓሜሁ ሊቅ ብሂል አይቴ ተኀድር::

፵. ወይቤሎሙ ንዑ ትርአዩ :: ወሖሩ ወርእዩ ኀበ የኀድር ወወዐሉ ኀቤሁ ይእተ ዕለተ እስከ ዓሥሩ ሰዓት::

## የምዕራፍ ፬ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ሀ) አርድእት ለዘይተልዉ ተስእሎታት ለእመ ኮኑ አማነ በሉ ርቱዐ ወለእመ ኢኮኑ አማነ በሉ ሕስወ።

፩) ወነገረ ስምየ ዮሐንስ የሚለው ሐረግ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ቁጥር ሠላሳ አንድ መግቢያ ነው።

፪) እዝን የአማርኛ ቋንቋ አቻው ጆሮ ነው።

፫)“ ዐፅም” አካል ዘታሕተ ክሣድ ውስጥ የሚጠቀስ ነው።

### ለ) አርድእት ኅረዩ ርቱዐ አውስኡት እምነ ዘተውሕቡ።

፩) ከሚከተሉት ውስጥ አካል ዘላዕለ ክሳድ ያልሆነው የቱ ነው።

ሀ) ምጕንጳ ለ)ሕልቅ ሐ) መንሰክ መ)ብረክ

፪) የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ቁጥር አርባ መደምደሚ ሐረግ

ሀ)አይቴ ተኀድር ለ) እስከ ዓሥሩ ሰዓት

ሐ)ወተለውዎ ለኢየሱስ መ)ወይቤሎሙ ንዑ ትርአዩ

፫) ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ “መሳውዕ” ለሚለው ቃል አቻ ፍቺው ምንድነው?

ሀ) ጎን ለ) ጅማት ሐ) ላንቃ መ) አንገት

### ሐ) ሀቡ ድልው አውስኡት ለዘይጠልዉ ተስእሎታት።

፩) ወልጡ ኀበ ልሳነ አምሃራ።

ምጕንጳ = ____________________

ፍጽም = ____________________

ጕርኤ = ____________________

አጽባዕተ እግር = ____________________

አንጉዕ = ____________________

ካቢ = ____________________

ጥብዕ =____________________

አጽብ = ____________________


፪) በግእዝ እና በአማርኛ ተመሳሳይ ስም ያላቸው የሰውነት ክፍሎች መካከል ቢያንስ ሦስቱን ጥቀሱ።

፩_ ____________________

፪ ____________________

፫ ____________________

፫ ቀጣዩን ሥዕል ተመልክታችሁ ቀስቶቹ የሚያመለክቱበትን ቦታ በግእዝ ስማቸውን ቀስቱ ላይ ጻፉ?



# ምዕራፍ ኀምስቱ

## ቀለማት አልባሳት ትዕምርተ መካናት

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

. የቀለማትን ዓይነትና የግዕዝ መጠርያ በግእዝ ይለያሉ፤

. የተወሰኑ አልባሳት መጠርያዎችን በግእዝ ያውቃሉ፤

. አራቱን አቅጣጫዎች በልሳነ ግእዝ ይለያሉ፤

### ተስእሎታተ መራኁት(የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. አረንጓዴ ቀለም  በግእዝ ቋንቋ ምን ይባላል?

፪. ጫማ በግእዝ ምን ተብሎ ይጠራል?

## አስማተ ቀለማት

ብስንሶ - አረንጓዴ


እለቄጥሩ - ቢጫ

ቀዩሕ - ቀይ

ሰማያዊ - ሰማያዊ



ጸሊም- ጥቁር



ጸዓዳ - ነጭ

## አልባሳት



ቀሚስ - ቀሚስ



ቆጽን - ጫማ




ድንታር - ቀበቶ



ናዕል - ካልሲ

## ትዕምርተ መካናት

### ላዕል - ላይ



ፀጋም - ግራ

የማን - ቀኝ

### ታሕት - ታች

## ዋቢ መጽሐፍ

፩. ወንጌል ዘዮሐንስ